ለራድዮ ሰላም

ኦገስት 13 1994

## የሰላም ችግር በኢትዮጵያ

## አጥፊ የፖለቲካ አዙሪት

ባለፈው ፕሮግራማችን እንደጠቆምነው ለዘመናት የኢትዮጵያን ህዝቦች ፋታ ነስተው ሲያዋክቧቸው የኖሩትና ዛሬም እየሰፉ ሊሄዱ የሚችሉት ግጭቶች እጅግ ብዙ መነሾዎች አሏቸው::በእነዚህ ባላቋረጡ ግጭቶች ሳቢያ ሃገራችን ከከፈለችው የደምና የአንባ ግብር ባሻገር ሌላ አሳሳቢ ብለን የጠቀስነው በነዚሁ ግጭቶች መበራከትና አለማቋረጥ የተነሳ ህብረተሰባችን ቀስ በቀስ ጥፋት ሌላ ጥፋትን እየወለደ፣ ጥፋትና ጥፋት እየተጋገዙ የሚያድጉበት አደገኛ አዙሪት ውስጥ መዘፈቃን ነው::

እነዚህ የጥፋት አዙሪቶች የምንላቸው ክስተቶች የኢትዮጵያን ህዝቦች እንዴት ማለቂያ ለሌለው መከራ እንደዳረጓቸው ሲያብራራ ለታህሳሱ የሰላምና እርቅ አገር አቀፍ ጉባኤ በአስተባባሪው ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የቀረበው ሰነድ እንደሚከተለው ይላል

"የኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ የሰላም ፋታ፣ የዴሞክራሲና የማህበራዊ ፍትህ ፍንጭ ተነስተው ለዘመናት በመቆየታቸው ሃገራችን የርሃብ፣ የስደት፣ የኋላ ቀርነትና የጭቀና ቋት እንደሆነች ለሁላችን ግልጽ ነው:: የዴሞክራሲ መጥፋት፣ ኋላ ቀርነት፣ የማህበራዊ ፍትህ መጓደል የሚቀሰቅሷቸው ግጭቶች ድህነታችንን፣ ኋላ ቀርነታችንን፣ ጭቀናንና ፍትህ አልባነትን እያባባሱ፣ ይህ ደግሞ ሁኔታዎችን ለሌሎች ግጭቶችና ጦርነቶች እያመቻቸ ህብረተሰባችን እንደዚህ አውተብትበው እጅ ከወርች ካሰሩት የጥፋት አዙሪቶች ለመላቀቅ ፋታ ተነስቶ ሲዋከብ ለዘመናት ቆይቷል::"

ከነዚህ ሁሉ አሳሳቢ የሆነውና አንድ ቦታ ላይ እንደምንም ካልተሰበረ የኢትዮጵያችን ችግሮች ከመፈታት ይልቅ እየተባባሱ እንዲሄዱ የሚያደርጋቸው በፖለቲካው መስክ የተከማቸው አሉታዊ ባህል ነው:: ሃገራችን አልፎ አልፎ ብልጭ ድርግም ካሉ ወቅቶች በስተቀር የህዝቦቿን ደህንነትና ብልጽግና ከራሳቸው ጥቅም አስቀድመው የሚያስተዳድሯት አገዛዞች ያገኘችበት ወቅት እምብዛም ነው:: በየጊዜው ለስልጣን የሚቀናቀኗቸውን ኃይሎች በጦር ኃይል አሸንፈው አገዛዝ የጨበጡ አገዛዞች በኃይል መጥተው፣ በኃይል ለመደላደል ሞክረው፣ ይህ አልሳካ ሲል በእብሪት ከደነፉበት አደባባይ ከነሱ ባየለ አመጽ እስኪወገዱ ድረስ ለዘመናት የተፈራረቁብን አገዛዞች የሰላምና የእርምጃችን ጠንቅ እንደሆኑ ያለፉ አገዛዞች ሆነው እናገኛቸዋለን::

«ዴሞክራሲ ቢጠፋ፣ ፍትህ ቢጓደል፣ የሰላማዊ ጨ ትግል በር ቢዘጋብኝ በአራት ሰባራ ጠመንጃ የብረት ትግል አንስቼ ለዚህ በቃሁ» የሚለን የኢህአዴግ አመራር ካሳለፍነው የጥፋት ሂደት ዘመን ቅንጣት ትምህርት የቀሰመ ኃይል አይደለም:: የገባንበትን የጥፋት አዙሪት ገዥዎችም ሆኑ ተገዥዎች በሃገርና በህዝብ ፍቅር መንፈስ በጥሞና ተወያይተው መስበርና በታሪካችን አይተነው ሰምተነው የማናውቀው አዲስ ጅማሮ መቀስቀስ በሚገባበት ወቅት በተለይ በዚህ አንጻር ብዙ የአመራር አደራ የሚጠበቅበት በሥልጣን ላይ ያለው ኃይል ሰላማዊ ትግሉ ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን:: የኢትዮጵያ ህዝብ መከራ፣ ርሃብ፣ ኋላ ቀርነት፣ ድህነት እንደሬት መርት ወደሰላምና ዴሞክራሲ በሚያደርገው ጉዞ ከፊት ከፊት ሆነው ይመሩናል ብሉ የጠበቃቸው ኃይሎች እስከናካቴው ከበስተኋላ ሆነው እንደከብት ሊነዱት የሚሞክሩ እጅግ ኋላ ቀር ኃይሎች ሆነው አግኝቷቸዋል::

በተለይ ዛሬ ደፍን አፍሪካ በዴሞክራሲ አገዛዞች እየተላበሰች በምትሄድበት የታሪክ ወቅት የኢትዮጵያን ህዝቦች ከዚህ ሂደት ገንጥሎ የዴሞክራሲንና የሰላምን ጸጋ ሊነፍጋቸው በመሞከር ላይ ያለው እጅግ ኋላ ቀርና ባረጀ በሬ ለማረስ የሚሞክረው የኢህአዴግ አመራር ተልቅ ክስረት ካለፈው አለመማሩ ብቻ አይደለም::እንደማገኘውም ህብረተሰብ

የኛም ህብረተሰብ ባህል ክፉም ደግም የያዘ እንደመሆኑ መጠን አንዳንዴ ልብ ብሎ ለሚታዘብ ዜጋ ይህ በሃገራችን የተጫነው ኃይል ከዚህ ባህላችን አሉታዊ ገጽታዎች ብቻ እንደ ዘር ተሰባስበው የሰፈረበት አሉታዊ ኃይል መሆኑ ነው ወይ? ብሎ ራሱን መጠየቁ ይገደዳል የሆነ ሆኖ ግን አንድ በርግጥ መናገር የምንችለው ጉዳይ አለ:: ካለፈው ትምህርት አልቀሰመም የምንለው የኢህአዴግ አመራር ህብረተሰባችን ለዘመናት ተውተብትቦ የተያዘበትን የፖለቲካ የጥፋት አዙሪት እድሜ ለማራዘም የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ያው ያረጁ ያፈጁ ዘዴዎች እንደሆኑ ሩቅ ሳንሄድ የዚህን ክፍለዘመንና የተፈራረቁበንን አገዛዞች ሁኔታ መመልከት ብቻ ይበቃል::

በሰላም ወደሰላምና ዴሞክራሲ እንዳንጓዝ በገዥዎቻችን የአርቆ አስተዋይነት ማነስ የተነሳ በሩ ተዘግቶ የገዥዎች አመጽ የተገዥዎችን አመጽ እየጋበዘ አገራችን እንደዚህ ለጥፋት ስትዳረግ የቆየችበት የፖለቲካ የጥፋት አዙሪት በዝርዝር ሲታይ ሶስት የማይነጣጠሉ ገጽታዎች አሉት::

1ኛ/ከአጼ ኃይለሥላሴ እስከ አቶ መለስ ዜናዊ የተፈራረቁበን አገዛዞች ማንኛውንም የፖለቲካ ለውጥ በር ጥርቅም አርገው ከመዝጋት አልፈው በጊዜው በጦር ኃይል ያገኙትን የበላይነት ከነሱም አልፈው ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚሞክሩ አገዛዞች ነበሩ://አጼ ኃይለሥላሴ የልጅ እያሱን መንግሥት ገልብጠው ሰገሌና ቶራ መስክ ላይ በተቀዳጁት ድል የተጀመረው የበላይነት ጉዞ ከአስራ ሶስት ዓመት ትርምስ በኋላ በመጋቢት ወር 1922 በራስ ጉግሣ ጦር ላይ በተቀዳጁት ድል እልባቱን አገኘ::ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውዱን እንደተቀዳጁ በደነገጉት ህገመንግሥት ለማስረገጥ የሞከሩት የዘውድ አገዛዝን ብቻ ሳይሆን የሳቸውን ዘር አገዛዝ ዘላለማዊነት በመሆኑ ይህ ህገመንግሥታቸው አንቀጽ 2 የዘውዱ አወራረስ እስከዘላለም ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘር እንዳይወጣ ይደነግግ ነበር:://ደርግ/ኢሰፖ ይህ ነው በማይባል ጭፍጨፋ የአንድን ትውልድ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ጨርሰው የበላይነታቸውን በዘላቂ ሁኔታ ያረጋገጡ ሲመስላቸው ለዚህ የበላይነት እልባትና ህጋዊ ልባስ ለመስጠት በሃገራችን ላይ የጫኑት ህገመንግሥት እርግጥ ዘላለማዊ ነኝ አይልም:: ነገር ግን በዚሁ ህገመንግሥት «የሃገሪቱ የእድገት አቅጣጫ ቀያሽ፣ የመንግሥትና የመላው ህብረተሰብ ሆናለሁ ብሎ ራሱን የሾመው ኃይል ይህንን የበላይነቱን የሶሻሊዝም ግንባታው ለሚጠይቀው ከትውልድ ትውልድ ለማያልቅ ረዥም የታሪክ ወቅት ለማረጋገጥ የተደነገገ ነበር:: //የኢህአዴግ መሪዎችም ቀሸት ከዚህ ብዙ አይለይም::በመቋቋም ላይ ያለው የህገመንግሥት ጉባኤ የኢህአዴግ ጠቅላላ ጉባኤ ከመሆን እንደማያልፍ እያወቀ ነው፣ መጭው ህገመንግሥት ከኢህአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራምነት ሰፍቶ እንደማይሄድ እየተገነዘበ ነው፣ ይህ ሁሉ የሚሆነውና ሊሆን የቻለው አላፊ ጠፊ በሆነ የጦር የበላይነት መሆኑን ሳናጣው እነሱም እንዳለፉት አገዛዞች ስለዚህ ሰነድና ስለአገዛዛቸው ዘላቂነት ይቃዡሉ:: መጋቢት 28 1986 አቶ መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ህዝብ ባደረገው ንግግር በዚህ ቀሸት ዓለም ውስጥ የሚዋሸቅ መሆኑን ሲያረጋግጥ መጭው የኢህአዴግ ህገመንግሥት /ብሎም የኢህአዴግ የበላይነት/ ከዚህም ትውልድ አልፍ ለሚቀጥሉትም እንደሆነ በድፍረት እስከመናገር ደርሷል::

2ኛ/በዚህ መልክ በኃይልና ኃይለኞች በደነገጉት ህጋዊ ልባስ የተተከሉትን አገዛዞች በሰላማዊ መንገድ ለመቀየር የሚቻልበት ሁኔታ ተፈጥሮ አያውቅም::እርግጥ ባለፉት 60 ዓመታት የኢትዮጵያ ህዝብ ስለህገመንግሥትና ስለምርጫ ብዙ ያየና የሰማ ህዝብ ነው:: ግን ህገመንግሥታት የህዝብ ፍላጎት ውጤትና በገዥዎችም በተገዥዎችም ላይ የበላይነት ያላቸው የሃገር መተዳደሪያ ሰነድ ሆነው አያውቁም:: የምርጫ መሠረታዊ ትርጉም አንድ ህዝብ ያለን አገዛዝ ለመቀየር ወይም ደግሞ ያለን አገዛዝ ለተወሰነ ጊዜ ለማቀ

የት የሚካሄድ ህገመንግሥታዊ መብት መሆኑ ሲታወቅ ያለን መንግሥት ለማጽደቅ እንጂ ለመቀየር በሚያስችል ሁኔታ ምርጫዎች ተካሂደው አያውቁም:: ይህ ያልተቻለበት መሠረታዊ ምክንያት በርግጥም በህብረተሰቡ ውስጥ በቀዳሚያ ዲሞክራሲ እስካልሰፈነ ድረስ በምርጫ ብቻ ለውጥን ለማምጣት የማይቻል በመሆኑ ነው:: ከዚህ ዘልቀን ወደ ዝርዝር ምክንያቶች ስንገባ ደግሞ በምርጫዎችና በሰላማዊ ዘዴ ለውጥ ለምን እንዳልተቻለ ስንመለከት ሁለት ቁም ነገሮች እናያለን:: አንደኛ ባለፉት 60 ዓመታት የተካሄዱት ምርጫዎች ሁሉ የተካሄዱት በጊዜው የበላይነትን የያዙ አገዛዞች በደነገጓቸውና ለውጥን በማይፈቅዱ ህገመንግሥታዊ ክልሎች ውስጥ ነበር:: ሁለተኛ ምርጫዎቹ ሁሉ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በሉት አገዛዞች ሙሉ ቁጥጥር ሥር የተካሄዱ ምርጫዎች ናቸው:: ይህም በመሆኑ መራጭ ተመራጭ ማን መሆን እንደሚችል፣ ለዚህ መሠረታዊ የዜግነት መብት ብቁ የሚሆነው ማን እንደሆነ የሚወስኑት እነዚው አገዛዞቹ ናቸው::// የአጼ ኃይለሥላሴ የመጀመሪያው የምርጫ ህግ አንቀጽ 49 የመምረጥና የመመረጥ መብት የሚፈቀደው ለባለመሬቶች ብቻ ነው ብሎ የሚቁም አልነበረም:: አልፍ ተርፍ "በገንዘብ ብቻ የከበሩ ተርታ ሰዎች እንዳይወዳደሩ የተከለከለ ነው::" የሚል የምርጫ ህግ ነበር:://ደርግ ምንም እንኳን በህገመንግሥቱ አንቀጽ 50 ኢትዮጵያውያን በሙሉ የመምረጥና የመመረጥ መብት አላቸው ቢልም በተጨባጭ ለመመረጥ መብት ያላቸው የኢሰፖ አባላት ብቻ ነበሩ::// የዓለም አቀፉ ሁኔታና የአሳዳሪዎቹ ተጽእኖ ኢህአዴግን የብዙ ፖርቲዎች ዲሞክራሲን ሃሳብ ቢያንስ ከአንገት በላይ እንዲቀበል አስገድዶታል:: በምርጫዎች ተቃዋሚ ኃይሎችም መወዳደር ይችላሉ እስከማለት የተገደረደረ ኃይል ነው:: በተጨባጭ የምናየው ግን እዛው በዛው የሚያስቀም የሚያስለቅስም ሁኔታ ነው:: በኢህአዴግ ምርጫ ተቃዋሚዎች ሊሳተፉ ይችላሉ ቢገለፅም በህዝብ ፊት የሚገጥሙትን ወይም እንዳይገጥሙት የሚፈልጋቸውን ኃይሎች በቀዳሚያ የሚመርጠው ራሱ ኢህአዴግ ነው::

3፣/ ስስተኛና የሃገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ ሁልጊዜም አመጽን እንዲጋብዝ የሚያደርገው ችግር ለተጨባጭ ለውጥ የሚታገሉ ኃይሎች ዓላማቸውን በሰላም ለማራመድ አለመቻላቸው ነው:: አገዛዞቹ የለውጥ ኃይሎችን ለመቋቋም ራሳቸው በደነገጓቸው አዋጆችና ህግጋት ይጠቀማሉ:: ዛሬ ኢህአዴግ ሲያመቸው ብቻ እየጠቀሰ የሚቃወሙትን ዜጎች በፍርድ ቤት የሚሟገትበት የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ በአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት የተደነገገና ደርግ ወርስ ሲገለገልበት የነበረው ህግ መሆኑን ስናይ የተፈራረቁትን መንግሥታት በዚህ በኩል ምንም ዓይነት ልዩነት እንደሌላቸው እንገነዘባለን:: በሌላ በኩል ደግሞ ይህ የማያዋጣ ሲመስላቸው ለለውጥ የሚታገሉ ኃይሎችን ዓይን ባወጣ አፈና፣ ግድያ፣ ያለፍርድ ግዞት እየተጠቀሙ የማንናውንም የሰላማዊ ለውጥ ሂደት ለመቋቋም ተፍጨርጭረዋል:: አሁንም ኢህአዴግ በዚህ የዓመጽ ሂደት የተሰማራ ኃይል ነው:: ሃገራችንን ሰላም የነሳት ህዝቡ ጦር ጠማሽ፣ ዲሞክራሲያዊና ሃገር ወዳድ ታጋዮቿ አመጽ ናፋቂ ኃይሎች በመሆናቸው አይደለም:: በሃገራችን ሰላም የመጣው ህብረተሰባችን ከእለት እለት በይበልጥ እንደህይዎት እስትንፋስ እያስፈለገው የሚሄደውን ዲሞክራሲ ሲያመቻቸው በራሳቸው ህግ መሠረት ይህ ሳያመች ደግሞ በለየለት ዓመጽ በመጠቀም ለመቋቋም በጊዜያዊ ወታደራዊ የበላይነት አቅም የሚገኙ አገዛዞች ይህ ነው የማይባል [illegible] መፍጨርጨር በማድረጋቸው ነው::

የኢትዮጵያን ህዝቦች ሳይሆን ኢህአዴግን ብቻ ወደዘላቂ መንግሥትነት በማሸጋገር እያከተመ ያለው የሽግግር ዘመን ሃገሪቱን ወደዲሞክራሲ ሳይሆን ወደአንድ አናሳ ኃይል ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ፣ ወደሰላም ሳይሆን ወደባሰ ትርምስ ይዞ በመንጉድ ላይ ያለ የኪሳራ ሂደት የሆነው ይህንን የፖለቲካ አጥፊ አዙሪት ለመስበር የኢህአዴግ አመራር ምንም የረባ ርምጃ ባለመውሰዱ ነው:: በሚቀጥለው ፕሮግራማችን በዚህ ጉዳይ 'ሽግግሩና በእንጭጩ የተቀጨ ተስፋ' በሚል ርእስ በሰፊው እንመለስበታለን::

* ይህ አረፍተነገር ይስተካከል